# የመገናኛ ብዙሀን እና የጋዜጠኞች የምርጫ

# አዘጋገብ የስነምግባር ደንብ

# ቁጥር 6/2002 ዓ.ም

መገናኛ ብዙሀን በዴሞክራሲያዊ የምርጫ ሂደት ውስጥ መራጮችን በማበረታታት፣ ለመራጮች ውሳኔ የሚያግዙ የተሟሉ መረጃዎችን በማቅረብ፣ በሂደቱ ውስጥ ጉልህ ሚና መጫወት እና ከመንግስት፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና ከማንኛውም አካል ተወዳዳሪ ራሳቸውን ነፃና ገለልተኛ አድርገው በመንቀሳቀስ ፍትሀዊ፣ ሚዛናዊና ትክክለኛ ሪፖርትና ዘገባ ማቅረብ እንዲችሉ፣

የመገናኛ ብዙሀን ወይም ጋዜጠኞች የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት አካል በሆነው ምርጫ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ሙያዊ ስነምግባርን በተከተለ አኳኋን በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችላቸው አሠራር መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በተሻሻለው የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 ዓ.ም. አንቀፅ 59 (4)፣ 91 (4) እና 110 መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

## አንቀፅ 1 አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ «የምርጫ አዘጋገብ ስነምግባር ደንብ ቁጥር 6/2002 ዓ.ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## አንቀፅ 2 ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. **“መገናኛ ብዙሀን”** ማለት በየጊዜው የሚወጡ ህትመቶችንና ብሮድካስቶችን /የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያን/ የሚያካትት ሥራ ነው፡፡

2. **“ምርጫ ህግ”** ማለት የተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 ነው።

3. **“ቦርድ”** ማለት በምርጫ ህጉ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው።

4. **“ምርጫ ነክ መልዕክት”** ማለት ለምርጫ የሚወዳደር ፓርቲ ድምፅ ሰጭዎችን ለማግባባት የሚያቀርበው የምረጡኝ መልዕክቶች እና በተወዳዳሪዎች የሚቀርብ ማንኛውም ትችትና አስተያየት ነው።

5. **“የፖለቲካ ማስታወቂያ”** ማለት ለምርጫ ውድድር የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ ገንዘብ በመክፈል ወይም ለመክፈል ቃል በመግባት በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን ወይም በጋዜጣ የሚያስነግረው ማስታወቂያ ነው።

6. **“የፖለቲካ ፓርቲ”** ወይም **“የፖለቲካ ድርጅት”** ማለት ከሕብረተሰቡ ውስጥ የተወሰኑ ሰዎችን በማሰባሰብ የራሱን የፖለቲካ እምነትና ዓላማ የሚያንፀባርቅበት ፕሮግራም በማውጣት በሀገር አቀፍ ወይም በክልል የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ በህግ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ ማኅበራዊ ተቋም ነው፡፡

7. **“የምርጫ ወቅት”** ማለት ቦርዱ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ የመጨረሻው የምርጫ ውጤት በይፋ በቦርድ እስከሚገለፅበት ያለው ጊዜ ነው፡፡

8. **“የምርጫ ዜና ወይም የወቅታዊ ጉዳዮች ዘገባ”** ማለት አገራዊ ወይም ዓለምአቀፋዊ ይዘት ያላቸው ፖለቲካዊ፤ ማህበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ምርጫ ነክ ሁነቶች ላይ የሚያተኩር ወይም በእነዚህ

ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ ትንታኔዎችን፣ አስተያየቶችን የሚያካትት ነው።

9. "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሠጠው አካል ነው።

**አንቀፅ 3** <u>አላማ</u>

የዚህ ደንብ አላማ ህጋዊ፣ ሰላማዊ፣ ነፃ፣ ፍትሀዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማካሄድ የሚያስችል የተሟላና ትክክለኛ መረጃ መራጩ ህዝብ እንዲያገኝ ማስቻል ነው።

**አንቀፅ 4** <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ሀገሪቱ ውስጥ በሚካሄድ ማንኛውም ምርጫ ምርጫን አስመልክቶ ዜና፣ ዘገባ፣ ሪፖርት ወይም መረጃ በሚያቀርቡ፣ በሚያስተላልፉ ወይም በሚያሠራጩ ማናቸውም ጋዜጠኞች ወይም የመገናኛ ብዙሀን ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

**አንቀፅ 5** <u>የምርጫ ሂደትን ለመከታተል ጥያቄ ማቅረብ ስለሚችሉ የመገናኛ ብዙሃን</u>

ማናቸውም የመገናኛ ብዙሀን በሀገሪቱ ውስጥ የሚካሄዱ ምርጫዎችን በሚወክሏቸው ጋዜጠኞች አማካይነት ለመከታተል የእውቅና ካርድ ጥያቄ ለቦርዱ ማቅረብ ይችላሉ።

**አንቀፅ 6** <u>የመገናኛ ብዙሀን ኃላፊነት</u>

1. የመገናኛ ብዙሃን ሁሉም ተ□□ሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች አላማቸውን ለመራ□ ሕ□ብ የማቅረብ ፍትሃዊ እድል እንዲያገኙ እና የመራጩን አማራጭ የፖሊሲ ሀሳብ የማግኘት እና የማመዛዘን እድሉን ማስፋት አለባቸው።
2. መገናኛ ብዙሃን የሚያቀርቧቸው ከምርጫ ጋር የተያያዙ ዜናዎች፣ ዘገባዎች፣ ሪፖርቶች እና ወቅታዊ

ፕሮግራሞች ማንኛውንም ፓርቲ ከመደገፍ ወይም ከማጥላላት የተቆጠቡ ከሕትመቱ ወይም ከፕሮግራሙ አዘጋጆች አስተያየትና አቋም የፀዱ ወቅታዊ፣ ገለልተኛ ሚዛናዊና ትክክለኛ መሆን አለባቸው፣

3. ማናቸውም የብዙሃን መገናኛ የተለያዩ አስተሳሰቦች፣ አመለካከቶችና ትችቶች ማስተላለፊያ እንዲሁም የመከራከሪያና የመወያያ መድረክ ሆነው ለማገልገል መጣር አለባቸው።

4. የመገናኛ ብዙሀን በፓርቲዎች መካከል የክርክር መድረክ በሚያዘጋጁበት ወቅት ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ቀረቤታ ያላቸውን ኤክስፐርቶች፣ እንዲሁም ሌሎች ገለልተኛ የብዙሃን እና የሙያ ማህበራት የተውጣጡ የጠያቂዎች ቡድን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፣

5. በማናቸውም የመገናኛ ብዙሃን ዘገባ ውስጥ ፍሬ ነገሮችና አስተያየቶች በግልጽ ተለይተው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ማንኛውም ምርጫ ነክ ዘገባዎች ወይም ሪፖርቶች ጋዜጠኞች ከምንጩ የተገነዘቡት ፍሬ ነገር እንዳለ የሚያንፀባርቁ መሆን አለባቸው፡፡

6. የመገናኛ ብዙሃን ባለቤቶች በተቻለ መጠን በምርጫ ነክ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ሽፋን መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

7. ስለመራጮች መብት መረጃ በማቅረብ እና በመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ሂደት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማድረግ የሚጠበቅባቸው የመገናኛ ብዙሀን ከሚከተሉት አካላት የሚደርስባቸውን ቀጥተኛም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነ ጫና ማስወገድ አለባቸው፣

   ሀ/ የመገናኛ ብዙሀኑ ባለቤት፣

   ለ/ ከመንግስት፣

   ሐ/ ከማስታወቂያ ድርጅት፣

መ/ ገንዘብ ወይም ድጋፍ ከሚሰጠው ሰው ወይም ከደንበኛው ወይም

ሠ/ ከሌላ ማንኛውም ድርጅት ወይም ሰው

8. መገናኛ ብዙሃን በምርጫ ወቅት ለሚዘጋጁ የውይይትና የክርክር ፕሮግራሞች እንደዚሁም ለሚካሄዱ ቃለምልልሶች ተገቢውን የዜና ሽፋን መስጠት አለባቸው።

9. የመገናኛ ብዙሀን ሚናቸውን የሚወጡበት መንገድ፣

ሀ. የምርጫ አስፈፃሚ አካላት መልዕክቶችን፣ የስነዜጋና የመራጮች ትምህርትን ወይም መረጃዎችን፣

ለ. የፖለቲካ ፓርቲዎችን እና የእጩ ተወዳዳሪዎችን የፖለቲካ መልዕክት ወይም ማስታወቂያ ወይም የምርጫ ቅስቀሳን፣

ሐ. የምርጫ ዜናና ወቅታዊ ፕሮግራምን፣

መ. አጠቃላይ የምርጫ ሂደትን

ሙያዊ ስነምግባርን በማክበር ለመራጩ እና ለህዝቡ በማስተላለፍ ወይም በማሠራጨት ይሆናል።

## አንቀፅ 7 <u>የምርጫ ሂደትን የመከታተል መብት እና አጠቃላይ ቅድመ ሁኔታ</u>

1. በዚህ ደንብ የተደነገገውን መመዘኛ የሚያሟሉ ማናቸውም የመገናኛ ብዙሀን ወይም ጋዜጠኞች ቦርዱ የሚሰጣቸውን መታወቂያ በመያዝ የምርጫ ሂደትን ለመከታተል ይችላሉ።

2. ማናቸውም የመገናኛ ብዙሃን ወይም ጋዜጠኞች ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰ ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ምርጫውን ከሚያደናቅፍ ማንኛውም ተግባር

እንደዚሁም በምርጫው ሂደት ጣልቃ ከመግባት መቆጠብ አለባቸው።

3. ማናቸውም የመገናኛ ብዙሃን ወይም ጋዜጠኞች የምርጫው ውጤት በይፋ ከመገለፁ በፊት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጪ ሆኖ ስለምርጫው ውጤት አስተያየት መስጠት የለባቸውም።

4. ማናቸውም ምርጫን የሚከታተሉ ጋዜጠኞች ወጪ የሚሸፈነው በራሳቸው ወይም በወከላቸው ተቋም ይሆናል። የቦርዱን ተሽከርካሪ ወይም ሌላ ሀብት የመጠቀም መብት የላቸውም።

5. ማናቸውም የመገናኛ ብዙሀን ተቋማት የወከሏቸው ጋዜጠኞች ተግባራቸውን ከመጀመራቸው በፊት፡-

ሀ. ስለ ምርጫ ሂደቶች፣

ለ. በምርጫ ህጎች እና አሠራሮች እንደዚሁም

ሐ. በዚህ የስነምግባር ደንብ ድንጋጌዎች ላይ

የተሟላ ስልጠና እንዲያገኙና በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ አለባቸው።

6. ማናቸውም ጋዜጠኞች □□□ቡትን ጉዳይ ወይም ግድፈት በየደረጃው ለሚገኙ የምርጫ አስፈፃሚ አካላት በማቅረብ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ይችላሉ።

7. ማናቸውም የእውቅና ካርድ የተሰጣቸው የመገናኛ ብዙሀን ወይም ጋዜጠኞች ከፍተኛ የሙያ ስነምግባር ሊኖራቸው ይገባል። ይህንን የምርጫ አዘጋገብ የስነምግባር ደንብ አክብረውና ተገዥ ሆነው ለመንቀሳቀስ መስማማታቸውን ለዚሁ ተግባር በቦርዱ የተዘጋጀውን ቅፅ በመሙላት እና በፊርማቸው በማረጋገጥ ለቦርዱ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

8. የመገናኛ ብዙሀን ተቋማት የወከሏቸው ጋዜጠኞች ይህንን የስነምግባር ደንብ አክብረው እንዲንቀሳቀሱ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀፅ 8 ስለ ማመልከቻ አቀራረብ እና ፍቃድ አሰጣጥ

1. ማናቸውም የምርጫ ሂደትን መከታተል የሚፈልጉ የመገናኛ ብዙሀን የእውቅና ካርድ እንዲሰጣቸው ጥያቄያቸውን በፅሁፍ ለቦርዱ ማቅረብ ይችላሉ።
2. ማናቸውም የምርጫ ሂደትን ለመከታተል የሚቀርብ የእውቅና ካርድ ጥያቄ ማመልከቻ ቦርዱ የምርጫ የጊዜ ሠሌዳ ካወጣበት ቀን ጀምሮ ድምፅ የሚሰጥበት ዕለት 15 ቀን እስኪቀረው ድረስ መቅረብ አለበት።
3. ቦርዱ ለቀረበለት የእውቅና ካርድ ጥያቄ ማመልከቻው ተሟልቶ በደረሰው በሰባት ቀን ውስጥ በደብዳቤ ምላሽ ይሠጣል።
4. ቦርዱ የቀረበለትን የእውቅና ካርድ ጥያቄ መርምሮ መመዘኛውን አሟልቶና ብቁ ሆኖ ለተገኘ የመገናኛ ብዙሀን እና ጋዜጠኛ የእውቅና ካርድ እና መታወቂያ ካርድ ይሰጣል።

## አንቀፅ 9 የማመልከቻ ይዘት

ቦርዱ ማመልከቻ የሚቀርብበትን ቅፅ /ፎርም/ የሚያዘጋጅ ሲሆን፣ ምርጫ ለመከታተል ጥያቄ የሚያቀርቡ የመገናኛ ብዙሀንም በማመልከቻቸው ውስጥ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርባቸዋል።

1. የተቋሙን ስምና አድራሻ፣
2. የተቋሙን ባለቤት ስም፣
3. በተቋሙ የሚከናወኑ የሚሸፈኑ ስራዎች /መከታተል የሚፈልገው የምርጫ ሂደት/፣

4. ምርጫውን የሚከታተሉለት ጋዜጠኞች ስም ዝርዝር፣
5. የጋዜጠኞች ቡድኑን የሚመራው ጋዜጠኛ ስም እና አድራሻ፣
6. የውጭ ጋዜጠኞች ከሆኑ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡበት ቀን፡፡

## አንቀፅ 10 <u>ከማመልከቻ ጋር ተያይዞ ስለሚቀርብ ሰነድ</u>

የመገናኛ ብዙሀኑ ከሚያቀርቡት የማመልከቻ ቅፅ ጋር የሚከተሉት ሰነዶች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው።

1. የጋዜጠኛውን ስም፣ ዜግነት፣ የትውልድ ቀን፣ ቦታ እና ሌሎች የፓስፖርት ወይም የመታወቂያ መረጃን፣ ጋዜጠኛው በተግባሩ ዙሪያ በቂ ስልጠና □□ኘ መሆኑን እና ቦርዱ ያወጣውን ወይም ያፀደቀውን የስነምግባር ደንብ አክብሮ ለመንቀሳቀስ ፈቃደኛ መሆኑን የሚገልጽ በእያንዳንዱ ጋዜጠኛ ፊርማ የተረጋገጠ ሠነድ /ቅፅ/።
2. የመገናኛ ብዙሀኑ ቦርዱ ያወጣውን የስነምግባር ደንብ አክብሮ ለመንቀሳቀስ ፈቃደኛ መሆኑን የሚገልጽ በተቋሙ ማህተምና የበላይ ኃላፊ ፊርማ የተረጋገጠ ሰነድ።
3. ከላይ በንዑስ 1 ከተጠቀሰው እያንዳንዱ ጋዜጠኛ ካረጋገጠው ቅጽ ወይም ሰነድ ጋር ተያይዞ የሚቀርብ የጋዜጠኛውን ሙሉ ስም እና የወከለውን የመገናኛ ብዙሃን ስም በጀርባው የያዘ ጋዜጠኛው በቅርብ ጊዜ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት ፎቶግራፍ።
4. የጋዜጠኛው ፓስፖርት ወይም ሌላ የመታወቂያ ካርድ።

## አንቀፅ 11 ማመልከቻ ውድቅ የሚሆንባቸው ምክንያቶች

አንድ የመገናኛ ብዙሀን ወይም ጋዜጠኛ እንደአግባብነቱ በሚከተሉት ምክንያቶች ምርጫን የመዘገብ የእውቅና ካርድ አያገኝም፣

1. የማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ የሚቀርብ የእውቅና ካርድ ጥያቄ፣
2. ያልተሟላ ወይም የተሳሳተ /ትክክለኛ ያልሆነ/ ማመልከቻ፣
3. የእውቅና ካርድ የማቅረብ መብት በሌለው ሰው የቀረበ ማመልከቻ፣
4. ጥያቄውን ያቀረበው ተቋም ወይም ጋዜጠኛ የህግ ችሎታ የሌለው ከሆነ፡፡

## አንቀፅ 12 መታወቂያ ካርድ ስለመስጠት

1. ቦርዱ ዕውቅና ለሰጣቸው ጋዜጠኞች መታወቂያ ካርድ ያዘጋጃል፣ ይህንንም ጋዜጠኞቹን ለወከለው ተቋም ይልካል ወይም ጋዜጠኞቹ በአካል ከቀረቡ ለራሳቸው ወይም ለተቋሙ ህጋዊ ወኪል ይሰጣል።
2. የመታወቂያ ካርዱ የሚከተሉትን ነጥቦች የያዘ ይሆናል፣
   - ሀ. የቦርዱን ሎጎ /አርማ/፣
   - ለ. የወከለውን ተቋም ስም፣ እና የጋዜጠኛውን ፎቶግራፍ፣
   - ሐ. የጋዜጠኛውን ስም፣
   - መ. የቦርዱን ማህተም፣
   - ሠ. መታወቂያው የሚፀናበት ጊዜ፣
   - ረ. የመታወቂያ ቁጥር፣
   - ሰ. ፈቃዱን የሠጠው ኃላፊ ፊርማ እና
   - ሸ. የባለመታወቂያው ፊርማ፡፡

## አንቀፅ 13 የምርጫ ሂደትን የሚከታተል ጋዜጠኛ መብት

ማናቸውም ምርጫን ለመከታተል ፈቃድ የተሰጣቸው የመገናኛ ብዙሀን ወይም ጋዜጠኞች እንደአግባብነቱ የሚከተሉት መብቶች ይኖራቸዋል፣

1. ከጋዜጠኛው የግል ደህንነት ጋር በተያያዘ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ያለቅድሚያ ማስታወቂያ ጥያቄ ባቀረበበት ቦታ ምርጫን የመከታተልና የመዘገብ።
2. ማንኛውም የምርጫ ሂደት ማለትም የመራጮች ምዝገባን፣ የእጩ ምዝገባን፣ የምርጫ ቅስቀሳን፣ የድምፅ አሰጣጥን፣ የቆጠራ ሂደትን እና የውጤት አገላለጽን የመከታተል እና የመዘገብ።
3. ከመንግስት፣ ከቦርዱና ከሌላ ከማንኛውም ሰው ተፅእኖ ውጪ በገለልተኛነት ሥራውን የማከናወን።
4. ከቦርዱና ከአካባቢ ባለስልጣናት እንደዚሁም በየደረጃው ከሚገኙ የምርጫ አስፈፃሚ አካላት መረጃና ትብብር የማግኘት።
5. የምርጫ እንቅስቃሴዎች ተጀምረው እስከሚጠናቀቁ ድረስ በማንኛውም ጊዜ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ በመገኘት የመራጮችን ምዝገባ፣ የመራጮች መዝገብ ለሕዝብ ክፍት የሚደረግበትንና ድምፅ የሚሰጥበትን ጠቅላላ ሂደት፣ የመራጮችን ምዝገባ የሚመለከቱ መረጃዎች በምስጢር መያዛቸውን እንዲሁም የድምፅ አሰጣጡን ምስጢራዊነት በማይጥስ ሁኔታ የመከታተል።
6. በድምፅ ሰጪነት የሚመዘገቡትን፣ ድምፅ ሰጪዎችን እና የምርጫ አስፈፃሚዎችን የሚያውክ ወይም የምርጫ አስፈፃሚዎችን ሥራ የሚያደናቅፍ እስካልሆነ ድረስ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ የመዘዋወር፡፡
7. በድምፅ ሰጪነት ለሚመዘገቡ፣ ለድምፅ ሰጪዎች፣ ለዕጩዎች ወኪሎች ወይም ለታዛቢዎች ወይም ለምርጫ

ጣቢያ ኃላፊዎች ከምርጫ ጣቢያው ውጭ ቃለመጠይቅ የማድረግ፡፡

## አንቀፅ 14 <u>የምርጫ ሂደትን የሚከታተል ጋዜጠኛ ግዴታ</u>

ሌሎች በህግ የተደነገጉ ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ምርጫን ለመከታተል የእውቅና ካርድ የተሰጠው የመገናኛ ብዙሀን ወይም ጋዜጠኛ የሚከተሉትን ግዴታዎች ማክበር ይጠበቅበታል፤

1. የሀገሪቱን ሉአላዊነት እንደዚሁም የህዝብን ሰብአዊ መብትና መሠረታዊ ነፃነት ማክበር፣
2. የቦርዱን፣ የምርጫ አስፈፃሚዎችን፣ የፀጥታና ደህንነት እንደዚሁም የሌሎች የመንግስት አካላትን ሚና እና ስልጣን ማክበር። ለሚሰጧቸው ህጋዊ መመሪያዎች እና ትዕዛዞች ተገዥ መሆን፣
3. ለምርጫ አስፈፃሚዎች ስለ ኃላፊነታቸው ምክር ወይም መመሪያ አለመስጠት፣
4. መራጩ፡ ድምፁን ለማን እንደሰጠ አለመጠየቅ፣
5. የህግ ጉዳዮችን በራሱ አለመተርጎም እና የምርጫ ሂደትን የሚመለከት ህጋዊ ያልሆነ መረጃ ወይም መመሪያ አለመስጠት፣
6. በሚስ□ር ድምፅ መስጫ ክፍል እና በድምፅ ቆጠራ ቦታ ካሜራም ሆነ ሌላ የድምፅ ወይም የምስል መቅረጫ መሳሪያ አለመጠቀም፣
7. ከአድልዎና ከወገንተኝነት በፀዳ አኳኋን ተግባራትን ማከናወን፣
8. የሚዘጋጀው ሪፖርትና ዘገባ በትክክለኛ መረጃ፣ ከወገንተኝነት በፀዳ የመረጃ ትንተና፣ በተጨባጭ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ እና የምርጫ ሂደት እውነታዎችን ወይም ፍሬ ነገሮችን ከግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን ማድረግ፣

9. የሀገሪቱን እና የአካባቢውን ባህልና ልምድ ማክበር፣
10. በቦርዱ የተሰጠውን የመታወቂያ ካርድ በሚታይ ቦታ አድርጎ መንቀሳቀስ እና በሚመለከተው አካል ሲጠየቅ ማንነቱን የሚያረጋግጥ ፓስፖርት ወይም መታወቂያ ማሳየት፣
11. ለማንኛውም ለመመዝገብ የቀረበ መራጭ፣ ድምፅ ሰጪ፣ የእጩ ወኪል፣ ታዛቢ ወይም ምርጫ አስፈፃሚ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ የመራጮች ምዝገባ፣ የመራጮች መዝገብ ምርመራ ወይም የድምፅ አሰጣጥ በመካሄድ ላይ እያለ ቃለ-መጠይቅ አለማድረግ፣
12. የመራጮች ምዝገባ መረጃዎች በሰነድ ላይ ሲሰፍሩ ወይም መራጩ በድምፅ መስጫው ወረቀት ላይ የምርጫ ምልክት ሲያደርግ፣ በፊልም አለመቅረፅ ወይም ፎቶግራፍ አለማንሳት ወይም ማንኛውንም ምስል፣ የተቀረፀ ፊልም ወይም አስተያየት የተቀዳበትን የድምፅ ክር በስውር እጁ አለማስገባት እና
13. የድምፅ ሰጪዎችን ምርጫ ምስጢራዊነት በሚነካ አኳኋን የመራጮችን መዝገብ፣ የመራጮችን ምዝገባ መታወቂያ ወይም ማንኛውንም ሌላ ሰነድ በፊልም አለመቅረጽ፣ ፎቶግራፍ አለማንሳት ወይም ኮፒ አለማድረግ

ናቸው፡፡

## አንቀፅ 15 <u>የእውቅና ካርድ ስለመሠረዝ</u>

1. ቦርዱ አንድ የመገናኛ ብዙሀን ወይም ጋዜጠኛ የምርጫ ሂደትን እንዲከታተል የተሰጠውን ፈቃድ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊያግድ ወይም ሊሠርዝ ይችላል፣

   ሀ. በስራ ላይ ያሉ ህጎችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን እና ሌሎች አሰራሮችን ጥሶ ሲገኝ።

ለ. ለማንኛ□ም እጩ ወይም ፖለቲካ ፓርቲ አድልዎ ፈፅሞ ወይም አሳይቶ ሲገኝ።

2. ቦርዱ ለመገናኛ ብዙሀን ወይም ለጋዜጠኛ የሰጠውን የእውቅና ካርድ ሲሰርዝ ወይም ሲያግድ ውሳኔውን የወሰደበትን ምክንያት በመጥቀስ ለሚመለከተው ሰው ማሳወቅ አለበት።

3. የመገናኛ ብዙሀኑ ወይም ጋዜጠኛው ምርጫን እንዲዘግብ የተሰጠውን የእውቅና ካርድ በቦርዱ ከተሰረዘ የተሰጠውን መታወቂያ ወይም የእውቅና ካርድ ወዲያውኑ መመለስ አለበት።

**አንቀፅ 16** <u>ስለምርጫ ነክ መልዕክቶችና ማስታወቂያ</u>

1. በዚህ ደንብ እና የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ከቦርዱ ጋር በመሆን በሚያወጣው የመንግስት የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም መመሪያ መሠረት ማንኛውም ተወዳዳሪ ፓርቲ በምርጫ ዘመቻ ወቅት በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት የምርጫ ነክ መልዕክቶችን ማስተላለፍ ይችላል።

2. ማንኛውም ፓርቲ የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ በፓርቲው ማህተም እና የበላይ ኃላፊ ፊርማ የተረጋገጠ ደብዳቤ ለሚመለከተው የመገናኛ ብዙሀን ማቅረብ ይኖርበታል፣

    ሀ. የፓርቲው ስም፣ በምርጫ ቦርድ የፀደቀለትን የመወዳደሪያ አርማ ወይም ምልክት፣

    ለ. ዋና ጽ/ቤቱ የሚገኝበትን አድራሻ፣

    ሐ. መልእክቱ እንዲተላለፍ የፈቀደው የፓርቲ ኃላፊ ስም፣

    መ. መልእክቱ በድምፅ መቅረጫ መሳሪያ አማካኝነት ወይም በቀጥታ ንግግሩን የሚያቀርበውን ወይም

በመልእክቱ ውስጥ የተካተቱትን ንግግሮች የተናገሩትን ሰዎች ስም፡፡

3. ማንኛውም ፓርቲ ለመገናኛ ብዙሀን እንዲሰራጭ ወይም እንዲታተምለት የሚልከው የምርጫ ነክ መልእክት፣

   ሀ. የሀገሪቱን የምርጫ ህግ እና የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነምግባር አዋጅን የሚቃረን ይዘት የሌለው መሆኑን፣

   ለ. ማንኛውም ህገ ወጥ ድርጊት እንዲፈፀም የማይቀሰቅስ፣ የማያነሳሳ ወይም ህገ ወጥ ድርጊት የማያበረታታና የማይደግፍ፣ የሰውን ልጅ መልካም ስምና ክብር የጠበቀ፣ የብሔር ብሔረሰቦችንና ህዝቦችን ማንነት ያከበረ መሆን

   ማረጋገጥ አለበት።

4. ማንኛውም የመገናኛ ብዙሃን ወይም ጋዜጠኛ ለስርጭት የቀረበለትን የምርጫ ነክ መልዕክት ከስርጭቱ በፊትም ሆነ በኋላ ፓርቲውን ሳያማክር ማረምም ሆነ ማስተካከል ወይም ኤዲት ማድረግ አይችልም።

5. በንዑስ አንቀፅ 4 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የመገናኛ ብዙሀኑ ከፓርቲው የቀረበለት የምርጫ ነክ መልዕክት የምርጫ ህግን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነምግባር አዋጅን፣ የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅን መገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅን ወይም ሌሎች ህግጋት የሚተላለፍ መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ካለው እንዲያሰራጭ የተጠየቀውን መልእክት አላስተላልፍም ማለት ይችላል።

6. የመገናኛ ብዙሃኑ በንዑስ አንቀፅ 5 በተጠቀሰው መሰረት ሊያስተላልፍ ያልቻለውን መልእክት በተመለከተ በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ጉዳዩን ላቀረበለት ፓርቲ መልእክቱን

የማያስተላልፍበትን ምክንያት በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

7. የመገናኛ ብዙሃኑ ከፓርቲው ቅድሚያ ፈቃድ ሳያገኝ በአሳታሚው አስቀድሞ የታተመን የምርጫ ነክ መልእክት በድጋሚ ሊያሳትም አይችልም።

8. ማንኛውም የፖለቲካ ማስታወቂያ በፕሮግራም ጣልቃ አይሠራጭም።

9. በፖለቲካ ማስታወቂያ የምረጡኝ ቅስቀሳ ማድረግ የተከለከለ ነው።

## አንቀፅ 17 <u>ስለ ፍትሀዊና ሚዛናዊ ሪፖርት እና ዘገባ</u>

አግባብ በሆነው ህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ጋዜጠኞች ወይም የመገናኛ ብዙሀን በምርጫ ወቅት፣

1. ፍትሀዊ፣ ሚዛናዊ እና ከወገንተኝነትና ከአድልዎ የፀዳ ሁሉ አቀፍ የሆነ ትክክለኛ ሪፖርት ወይም ዘገባ ማቅረብ አለባቸው።

2. ለተወዳዳሪ ፓርቲዎችና እጩዎች አቅም በፈቀደ መጠን ተደራሽ መሆን እና ፍትሀዊ የመገልገል እድል መስጠት፣ አንድ እጩ በሌላ እጩ ላይ ውንጀላ ወይም ክስ ካቀረበ በተቻለ መጠን ከሁሉም ወገኖች አስተያየት መጠየቅ እና ሚዛናዊ የሆነ ሪፖርት ወይም ዘገባ ማቅረብ አለባቸው።

3. አስፈላጊ መረጃዎችን መደበቅ የለባቸውም። ይሁን እንጂ ሙያው ወይም ህግ በሚጠይቀው ሁኔታና መጠን መረጃዎችን ወይም የመረጃ ምንጮችን በሚስጥር ጠብቀው መያዝ አለባቸው።

4. በምርጫ ሂደቱ ውስጥ ባለድርሻ ከሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት የተለያዩ አመለካከቶችን እና አስተያየቶችን ማሰባሰብ እንደዚሁም የፓርቲዎችን እና የእጩ

ተወዳዳሪዎችን አመለካከት በተቻለ መጠን በራሳቸው ቃላት የተነገረውን በቀጥታ ሪፖርት ማድረግ ወይም መዘገብ አለባቸው።

5. የፖለቲካ ፓርቲን ወይም የእጩ ተወዳዳሪን መረጃ ሆን ብሎ ማዛባት፣ መደበቅ፣ እውነቱን ሀሰት ወይም ሀሰቱን እውነት አስመስሎ ማቅረብ የለባቸውም፡፡

6. የማንኛውንም ፓርቲ ወይም እጩ አርማ ወይም ሌላ መለያና መቀስቀሻ ምልክት አድርገው ስራቸውን ማከናወን የለባቸውም፡፡

7. በእጩ ተወዳዳሪነት የቀረቡ ትኩረት ተነፍጓቸው የነበሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በተለየ ሁኔታ ማበረታታትና ማስተዋወቅ ይገባቸዋል፡፡

8. በምርጫ ዘመቻ ወቅት በተለያዩ ተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል ስለተፈጠረ አከራካሪ ጉዳይ ሲዘግቡ በማስረጃ ተደግፈው አድልዎን በማስወገድ የሁሉንም ወገን አቋም ባካተተ መልክ በሚዛናዊነት የቀረቡ መሆን አለባቸው፡፡

## አንቀፅ 18 <u>አመፅ፣ ብጥብጥ እና ግጭት ማነሳሳት የተከለከለ ስለመሆኑ</u>

ማናቸውም የመገናኛ ብዙሃን ወይም ጋዜጠኞች፡-

1. አመፅ የሚያነሳሳ ወይም ሽብርተኝነትን የሚያበረታታ፣
2. ዘርን፣ ሀይማኖትን፣ ፆታን፣ ቋንቋን፣ ፖለቲካዊ አመለካከትን፣ ማህበራዊ አመጣጥን (social background) መሠረት ያደረገ አድልዎ እና ልዩነት ወይም ብጥብጥ ወይም አመፅ ወይም የፖለቲካ አለመረጋጋትና ቀውስ የሚፈጥር ወይም የሚያባብስ
3. የምርጫ ሂደትን የሚያውክ ወይም የሚያስተጓጉል ተግባር

መፈፀም የለባቸውም፣

4. ሞት፣ አደጋ ወይም በህዝብ ንብረት ላይ ጉዳት የሚያስከትል፣ የብሔር ጥላቻ ወይም የፖለቲካ እና የህብረተሰብ አለመረጋጋትን የሚያነሳሳ እንዲሁም ለአመፅ፣ ለብጥብጥ፣ ለሁከትና ግጭት የሚዳርጉ ስሜት ኮርኳሪ ቋንቋዎችን፣ አገላለፆችን፣ ዘገባዎችን እና ሪፖርቶችን ማዘጋጀት፣ ማተም ወይም ማሠራጨት የለባቸውም።

## አንቀፅ 19 <u>እውነታን ስለማፈላለግ</u>

ማናቸውም የመገናኛ ብዙሀን ወይም ጋዜጠኞች፣

1. እውነታን አፈላልገው ለማቅረብ መጣር አለባቸው።
2. የተለያዩ ከምርጫ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ እውነታን ለማፈላለግ፣ የሚረዳ ሙያዊ ምርመራ የማካሄድ እና ግኝቱንም /እውነታውን/ ለህዝብ ይፋ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።
3. ምንጩን በሚያውቁት እውነታ ላይ ብቻ ተመስርተው ሪፖርት ወይም ዘገባ ማቅረብ አለባቸው።
4. የሚያትሙትና የሚያሰራጩት መረጃ ወይም ዘገባ የተሟላ፣ ትክክለኛ፣ ተጨባጭ፣ ሚዛናዊ፣ እና አጠቃላይ የምርጫ ሂደቶችን የሸፈነ ወይም የዳሰሰ መሆን አለበት።

## አንቀፅ 20 <u>በምርጫ ሂደቶች ላይ ትምህርት እና ገለፃ ስለማስተላለ□</u>

1. የመገናኛ ብዙሀኑ፤ ከቦርዱ ጋር በአጋርነት ወይም በትብብር በመስራት የስነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት ማስተላለ□ አለባቸው፡፡

2. የመገናኛ ብዙሀን ቦርዱ በሚያወጣው የስነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት ማኑዋል ይዘት ወይም በሚሰጠው መመሪያ መሠረት፣

   ሀ. በምርጫ ፖሊሲዎች እና ጥልቅ ምልከታ እና ውይይት በሚሹ ማናቸውም የፖለቲካ ጉዳዮች፣ ለመራጩ ህዝብ መረጃ በማስተላለ□፣

   ለ. ስለ ምርጫው ለህዝቡ መልዕክት በማስተላለ□ እና ተጨባጭ መረጃ በመስጠት፣

   ሐ. መረጃዎችና የመራጮች ትምህርት በተለያዩ ቋንቋዎች ተዘጋጅተው መሠጠታቸው እና የህዝብ ብዛታቸው አነስተኛ ወደ ሆነ የህብረተሰብ ክፍሎች መድረሳቸውን በማረጋገጥ እና

   መ. ሴቶችን፣ አካል ጉዳተኞችን እና ትኩረት ተነፍጓቸው የነበሩ ወገኖችን ወዘተ ማዕከል ያደረገ ፕሮግራም መዘጋጀቱን በማረጋገጥ

   ረገድ የተለየ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

3. መገናኛ ብዙሀኑ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ወይም በሚሰጠው መረጃ መሠረት ገለልተኛ በመሆን በሚከተሉት የምርጫ ሂደቶች ላይ ያተኮሩ ትክክለኛ የመራጮች ትምህርት ማስተላለ□ ይገባቸዋል፣

   ሀ. የመራጮች ምዝገባ መቼ እንደሚካሄድ፣
   ለ. መቼ፣ የት እና እንዴት ድምፅ እንደሚሰጥ፣
   ሐ. የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ በሚስጥር እንደሚካሄድ፣
   መ. መራጩ ህዝብ ከምርጫ ተግትሮው ጋር በተያያዘ ከማንኛውም ተ□እኖ የተጠበቀ መሆኑን፣
   ሠ. የድምፅ መስጠትን አስፈላጊነት፣
   ረ. ስለተለያዩ አካላት ሚና እና

ሰ. በምርጫ ህጉ በተካተቱ ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ።

## አንቀፅ 21 የመራጩን ፍላጐት ማዕከል ስለማድረግ

1. ማናቸውም ጋዜጠኞች ወይም የመገናኛ ብዙሀን መራጩ ሕዝብ ሊገነዘበው በሚችለው መልክ /ቅርፅ/ የምርጫ መረጃ መስጠት አለባቸው።
2. ማንኛውም መረጃ ወይም ዘገባ ወዘተ መራጩ ህዝብ ለሚያካሂደው ምርጫ ወይም ለሚወስደው ውሳኔ የሚረዳ ተያያዥ መረጃ ወይም ዘገባ መሆን አለበት።
3. የምርጫ ስነስርዓቶችን፣ ደንቦችን እና ፖሊሲዎችን አስመልክቶ የሚሰራጭ መረጃ የቦርዱን ኦፊሴላዊ መረጃ የሚያንፀባርቅ ወይም የያዘ መሆን አለበት።
4. ማናቸውም ጋዜጠኞች ወይም የመገናኛ ብዙሃን መራጩ ህዝብ ሀሳቡን እና አመለካከቱን በነፃነት እንዲገልፅ ማበረታታት እና ለዚህም የሚረዳ እድል መስጠት አለባቸው።

## አንቀፅ 22 የዲሞክራሲ እሴቶችን ማስተዋወቅ

ማናቸውም የመገናኛ ብዙሀን የሚከተሉትን የዴሞክራሲ እሴቶች ማስተዋወቅ □□በቅባቸዋል፣

1. ስለ ህግ የበላይነት፣
2. ስለ ተጠያቂነት፣
3. ስለ መልካም አስተዳደር እና
4. የመቻቻል መርህን ማስተዋወቅ::

## አንቀፅ 23 ስነዖታ

ማናቸውም ጋዜጠኞች እና የመገናኛ ብዙሀን፣

1. በሴቶች ላይ አድሏዊ የሆነ ወይም የጥላቻ እና የእምነት ማጣት አመለካከትን ለሚፈጥሩ ወይም ለሚያንፀባርቁ መረጃዎች ሽፋን መስጠት የለባቸውም።
2. የሴቶች ተሳትፎ የሚኖረውን ጠቀሜታ በማስተማርና የህዝቡን ግንዛቤ በማሳደግ ሴት እጩ ተወዳዳሪዎችን ማስተዋወቅ እና ማበረታታት አለባቸው።

## አንቀፅ 24 <u>ስለ ክፍያ</u>

1. የቦርዱ ማንኛውም የምርጫ መረጃ፣ ትምህርት ወይም ማስታወቂያ እና ፕሮግራም በክፍያ ወይም ያለ ክፍያ በመገናኛ ብዙሀን ይተላለፋል።
2. የመገናኛ ብዙሀኑ ከማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪ ለተመሳሳይ መልዕክት የሚጠይቁት የማስታወቂያ ክፍያ መጠን እኩል መሆን አለበት።
3. ማናቸውም የመገናኛ ብዙሀን የፖለቲካ ማስታወቂያ ያለ ክፍያ ማስተናገድ አይችሉም።
4. ለፖለቲካ ማስታወቂያ የሚጠየቀው ክፍያ ለንግድ ክፍያ ከሚጠየቀው ክፍያ መብለጥም ሆነ ማነስ የለበትም።

## አንቀፅ 25 <u>ህግን ስለማክበርና ስለማስከበር</u>

1. የመገናኛ ብዙሀን ህገመንግስቱን ወይም ሌሎች የሀገሪቱ ህጐችን የሚጥስ ይዘት ያለው የፓርቲ ወይም የእጩ ተወዳዳሪ ማስታወቂያ ወይም ፕሮግራም ወይም የምርጫ ቅስቀሳ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ ማተም ወይም ማሠራጨት የለባቸውም።
2. ማናቸውም የመገናኛ ብዙሀን ወይም ጋዜጠኞች ህገመንግስቱን እና ሌሎች የሀገሪቱን ህጐች ማክበር አለባቸው።

3. ማንኛውም የመገናኛ ብዙሀን በስህተት ጉዳት ያደረሰን መረጃ ለማስተካከል የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ አለባቸው።

4. ማንኛውም የመገናኛ ብዙሃን የምርጫ ህግን፣ ደንብና መመሪያ ባገናዘበ መልኩ ትክክለኛ መልዕክት ማስተላለፍ አለባቸው::

## አንቀፅ 26 የምርጫ ቅስቀሳን ማስተናገድ ወይም ማስተላለፍ የተከለከለ ስለመሆኑ

1. ማናቸውም የመገናኛ ብዙሀን እና ጋዜጠኞች ድምፅ የሚሰጥበት ቀን 48 ሰዓት ሲቀረው ጀምሮ ድምፅ መስጠት እስከሚጠናቀቅበት ሰዓት ድረስ የፓርቲዎችን ወይም የእጩ ተወዳዳሪ የምርጫ ቅስቀሳን ማተም ወይም ማሰራጨት ወይም መዘገብ የለባቸውም።

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የመገናኛ ብዙሀኑ ወይም ጋዜጠኞቹ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን ወይም እጩ ተወዳዳሪዎችን የሚያስተዋውቅ በእውቀት ላይ የተመሠረተ ምርጫ ለማካሄድ የሚረዳ መረጃ እና ትምህርት ለመራጮችና ለህዝቡ ማስተላለ□ ይችላሉ።

3. በምርጫው እለት በሚዘገቡ ዜናዎችም ሆነ ፕሮግራሞች ውስጥ በጋዜጣ በምስልም ሆነ በድምፅ ግብአቶች መራጮች ወይም የምርጫ ድምፅ ሰጭዎች ያስተላለፉትን ውሳኔ የሚገልጽና በሌሎች ድምፅ ሰጭዎች ውሳኔ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ይዘት ያለው ሕትመት ማተምና ማሰራጨት የተከለከለ ነው።

## አንቀፅ 27 ቅድመ ምርጫ ትንበያ

1. ማናቸውም የመገናኛ ብዙሃን ለመራጩ ጠቀሜታ ያለውን የተዘጋጀ የምርጫ ቅድመ ትንበያ መረጃ ሊያትሙ ወይም ሊያቀርቡ ይችላሉ። ይሁን እንጂ የመገናኛ ብዙሀኑ፣
   - ሀ. የህዝብ አስተያየት አሰባሰበው ትንበያውን ያካሄዱትን ድርጅቶች እና መቼ እንዳካሄዱ፣
   - ለ. ምን ያህል ህዝብ እንደተጠየቀ እንደዚሁም የትና መቼ እንዴት እንደተከናወነ፣
   - ሐ. የተጠቀሙበትን ስልት፣
   - መ. መጠይቁ ሲደረግ የቀረቡትን ጥያቄዎች ይዘት ቃል በቃል ምን እንደሆኑ እና
   - ሠ. በመስክ ስራ የተገኘ ዳታን በመለየት

   በሪፖርታቸው ማካተት አለባቸው።
2. ከላይ በንዑስ 1 የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ሰው በምርጫው እለት የምርጫ ውጤት ትንበያ መረጃ በማዘጋጀት ያሰራጨ፣ እንዲዘጋጅ ያደረገ ወይም በማንኛውም መንገድ ለህዝብ የገለፀ እንደሆነ በምርጫ ህጉ መሠረት ከአንድ አመት ባልበለጠ እስራት ወይም መቀጮ ይቀጣል።

## አንቀፅ 28 ስጦታ መቀበል የተከለከለ ስለመሆኑ

1. ማናቸውም ጋዜጠኞች ወይም የመገናኛ ብዙሀን
   - ሀ. በጉቦ፣
   - ለ. በስጦታ፣
   - ሐ. በጥቅማጥቅም
   - መ. በማንኛውም ሁኔታ በመደለል

   የምርጫ ዘገባ ወይም ሪፖርት ማቅረብ የለባቸውም።

2. ትራንስፖርትም ሆነ ሌላ ምንም አይነት መደለያ ከፓርቲዎች፣ ከፖለቲከኞች ወይም ከተመራጮች መቀበል የለባቸውም።

3. ከሚያዘጋጁት የዜና ሪፖርት ይዘት ጋር የተያያዘ ምንም አይነት የተስፋ ቃል መግባት የለባቸውም።

## አንቀፅ 29 <u>የስነምግባር መጓደል</u>

በዚህ ደንብና በሌሎች ህጐች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው እንደከፍተኛ የሙያ ስነምግባር መጓደል ተቆጥረው ከሚያስቀጡ ተግባራት መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፤

1. እውነታን ሆን ብሎ አዛብቶ በማቅረብ ጉዳት ማድረስ፣

2. የሰውን ክብር የሚጐዳ እውነት ያልሆነ ንግግር ወይም ገለፃ ማድረግ ወይም ፅሁፍ ወይም ህትመት ማተም፣

3. መሠረተ ቢስ ውንጀላ፣

4. ከስራው ጋር የተያያዘ ማንኛውንም አይነት ጉቦ ወይም ስጦታ መቀበል፡፡

## አንቀፅ 30 <u>ስለፖለቲካ ፓርቲዎች እና እጩ ተወዳዳሪዎች ኃላፊነት</u>

ማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪ፣

1. የመገናኛ ብዙሀን ነፃነት ማክበር አለባቸው።

2. ጋዜጠኞችን ማዋከብ፣ ሙያዊ ተግባራቸውን ማደናቀፍ ወይም ማወክ የለባቸውም፡፡

3. የያዙትን የስራ ኃላፊነት ወይም ስልጣን ተጠቅመው ፍትሀዊ ያልሆነ የመገናኛ ብዙሀን ተጠቃሚ ከመሆን መቆጠብ አለባቸው።

4. ለመገናኛ ብዙሀንም ሆነ ለጋዜጠኛ ምንም አይነት ስጦታ፣ ጉቦ ወይም የተስፋ ቃል መስጠት የለባቸውም።

5. የሌላ ፓርቲን ወይም እጩን አስመልክቶ የተገለፀ አቋምን እና መረጃዎችን አዛብቶ ማቅረብ የለባቸውም።

6. መገናኛ ብዙሃን በምርጫው ሂደት ተገቢ ሚናቸውን እንዲጫወቱ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለባቸው፤

7. ወኪሎቻቸው ወይም ደጋፊዎቻቸው በጋዜጠኞች ላይ ጥቃት፣ ማስፈራራት፣ አደጋ፣ ጫና እና ድብደባ እንዳያደርሱባቸው ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው።

8. በምርጫ ዘመቻ ወቅት መቻቻልና ነፃ ክርክር እንዲረጋገጥ ተገቢውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

## አንቀፅ 31 <u>ስለ ምርጫ አስፈፃሚ አካል ኃላፊነት</u>

1. ቦርዱ፦

   ሀ. የመገናኛ ብዙሀን፣ የጋዜጠኞች፣ የፓርቲዎችን እና የእጩ ተወዳዳሪዎች የመናገር ነፃነት ማክበር እና በህግ መሠረት ስራዎቹን ለመገናኛ ብዙሀን ተደራሽ ማድረግ አለበት።

   ለ. መረጃ በመስጠት ረገድ በመገናኛ ብዙሀን መካከል ልዩነት መፍጠር የለበትም።

2. አቅም በፈቀደው እና በህግ መሠረት ትብብር ማድረግ እና በየደረጃው የሚገኙ የምርጫ አስፈፃሚ አካላትም ተገቢውን ትብብር እንዲያደርጉ ማድረግ አለበት።

3. አንድ የምርጫ ጣቢያ ኃላፊ ለሚዲያ የሚሰጠው ማናቸውም ቃለ-መጠይቅ ከምርጫ ጣቢያው ውጭ መካሄድ ይኖርበታል።

4. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በቃለ-መጠይቁ ላይ ከመረጃ ጋር ለተያያዙ አጠቃላይ ጥያቄዎች ምላሽ ሊሰጥ ይችላል፤ ሆኖም በመረጃው ላይ ትንታኔና አስተያየት ማቅረብ ወይም መስጠት የለበትም፡፡

5. የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እና ሌሎች ተመሳሳይ አጠቃላይ የመረጃ ጥያቄዎች ላይ ምላሽ ሊሰጡ ይችላሉ፣

ሀ. የመራጮችን ምዝገባ፣ የመራጮችን መዝገብ ለሕዝብ ክፍት ማድረግና የድምፅ አሰጣጡን ሥነ ሥርዓት፤

ለ. በምርጫ ጣቢያው የተመዘገበውን እና ድምፅ የሰጠውን ሕዝብ ብዛት፤

ሐ. የምርጫ አስፈፃሚዎችን ተግባራትና የተሰጣቸውን ሥልጠና እና

መ. በሥራ ላይ ያሉ የሥነ ምግባር መመሪያዎችንና የአሠራር ደንቦችን

በተመለከተ ሊሆን ይችላል፡፡

6. የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ከዚህ በታች ያሉትን እና የመሳሰሉ ትንታኔዎችን ወይም አስተያየቶችን መስጠት አይኖርባቸውም፣

ሀ. የምርጫውን አጠቃላይ ውጤት፤ በምርጫ ጣቢያ፣ በምርጫ ክልል ወይም በክልል ደረጃ በታየው ውጤት ላይ ተመስርቶ መተንበይ፤

ለ. ድምፅ አሰጣጡ ስለሚያመላክተው አዝማሚያ ወይም ከድምፅ አሰጣጡ ስለሚጠበቀው ውጤት አስተያየት መስጠት፤

ሐ. ስለፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ስለዕጩዎች ወይም ስለምርጫው የፖለቲካ ትችት መሰንዘር፤

መ. በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ፣ ተገቢው ሥርዓት ስለመከበሩ አስተያየት መስጠትን፤ በሌሎች አከራካሪ ጉዳዮች ላይ ግምታዊ አስተያየት መስጠት ወይም ማቅረብ እና

ሠ. አለባልታዎችን በተመለከተ አስተያየት መስጠት የለባቸውም፡፡

7. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች በመገናኛ ብዙሃንና በጋዜጠኞች ላይም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀፅ 32 ስለ ደንብ መጣስ

1. ይህን ደንብ እና ሌሎች ህጎችን በሚጥስ ሰው ላይ እንደአግባብነቱ የሚከተሉት ህጋዊ ወይም አስተዳደራዊ እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

2. የተፈፀመው ጥፋት ቀላል ከሆነ፤

    ሀ. ማስጠንቀቂያ መስጠት፣

    ለ. ተበዳዩ በጉዳዩ ላይ ምላሽ ወይም አስተያየቱን መስጠት ከፈለገ እንዲሰጥ ማድረግ፣

    ሐ. የመገናኛ ብዙሃኑ ወይም ጋዜጠኛው ይቅርታ እንዲጠይቅ እና ይህንንም በየመገናኛ ብዙሀኑ እንዲያሰራጭ ወይም እትም እንዲያወጣ ማድረግ፣

    መ. ስህተቱ ታርሞ እና ተስተካክሎ ወዲያውኑ እንዲሰራጭ ወይም ታትሞ እንዲወጣ ማድረግ፡፡

3. በጋዜጠኛው የተፈፀመው ጥፋት በዲሲፕሊን የሚያስቀጣ ሆኖ ሲገኝ ቦርዱ ጋዜጠኛው ለሚሰራበት ተቋም አስፈላጊውን እርምጃ ወስዶ እንዲያሳውቀው ያደርጋል፡፡

4. ማንኛውም አስተዳደራዊ እርምጃ ከተፈፀመው ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት።

5. ጥፋቱ ተደጋጋሚና በከፍተኛ ሁኔታ /ደረጃ/ ሲፈፀም ጉዳዩን ለሚመለከተው በማቅረብ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

6. የመገናኛ ብዙሀኑ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በራሱ ተነሳሽነት ወይም ከባለጉዳዩ በሚቀርብለት ጥያቄ በሪፖርቱ ወይም በዘገባው ወይም ባዘጋጀው ዜና ወይም ወቅታዊ ፕሮግራም ውስጥ የተፈጠረውን ስህተት አስተካክሎ በራሱ መገናኛ ብዙሀን ሊያሰራጭ ይችላል።

7. የዚህ ደንብ የአንቀፅ 15 ድንጋጌ አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች መጠየቅን አያስቀርም፡፡

## አንቀፅ 33 <u>የተሻሩ ደንቦችና መመሪያዎች</u>

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ እና አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## አንቀፅ 34 <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በቦርዱ ከፀደቀበት ከጥር 10 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

መርጋ በቃና /ፕሮፌሰር/
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
ሰብሳቢ